# የጉምሩክ ዕቃ አወጋገድ መመሪያ ቁጥር

**176/2013**

ገቢዎች ሚኒስቴር

የካቲት 2012

Ethiopian Ministry of Revenues
Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1

# የጉምሩክ ዕቃ አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 176/2013

ኮሚሽኑ የተተወ ወይም በጊዜ ገደቡ ከጊዜያዊ ዕቃ መከማቻ ያልወጣ ወይም የተወረሰ ዕቃ ማስወገድ እንደሚችል በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 የተደነገገ በመሆኑ፤

በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች የሚወገዱበትን ሁኔታ መወሰን እና ወጥ የሆነ የዕቃ አወጋገድ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 61፣ 62 እና 180 (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ዕቃ አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 176/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፡-

1/ "የተተወ ዕቃ" ማለት አስመጪው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፈጽሞ እንደማይረከበው የጽሑፍ ማረጋገጫ የሰጠበት ወይም የመጋዘን የቆይታ ጊዜ ገደብ ያለፈበት ዕቃ ነው፡፡

2/ "የተወረሰ ዕቃ" ማለት የጉምሩክ ህግ በመተላለፍ ጥፋት የተፈጸመበትና በጉምሩክ የተወረሰ ዕቃ ማለት ነው፡፡

3/ "አደገኛ ዕቃ" ማለት በሰው ወይም እንስሳት ሕይወት ላይ እንዲሁም በእዕዋት ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑ ማረጋገጫ የቀረበበት ዕቃ ነው፡፡

Ethiopian Customs Commission
Documentation No.1

4/ “የሚበላሽ ዕቃ” ማለት ዕቃው ከመለቀቁ ወይም ከመወገዱ በፊት በቀላሉ ሊበላሽ ወይም ከጥቅም ውጪ ሊሆን ይችላል ተብሎ በኮሚሽኑ የታመነበት ዕቃ ነው፡፡

5/ “የቁም እንስሳት” ማለት በህገወጥ መንገድ ሲንቀሳቀሱ የተያዙና በህይወት ያሉ የቤትም ሆነ የዱር እንስሳት ናቸው፡፡

6/ “የከበረ ማዕድን” ማለት በማዕድን አዋጅ በተሰጠ ትርጉም የሚሸፈን ዕቃ ማለት ሲሆን የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር በመመሪያ የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ማዕድን ይጨምራል፡፡

7/ “ገንዘብ” ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለው በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለመግዛት የሚያገለግል የገንዘብ ኖት ሲሆን ላምጪው ክፍያ የሚፈጸምባቸው የንግድ የክፍያ ሰነዶችን /Commercial Instruments/ ይጨምራል፡፡

8/ “ዕቃ ማስተላለፍ” ማለት ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች ወይም ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲተላለፉ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ዕቃዎች ለነዚሁ አካላት እንደሁኔታው በክፍያ ወይም ያለክፍያ ማስረከብ ነው፡፡

9/ “ዕቃ ማውደም” ማለት ጥቅም ላይ የማይውል ወይም ለገበያ የማይቀርብ ዕቃን በማቃጠል፣ በመቅበር፣ በማፍሰስ፣ በመሰባበር ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ እንዳይውል ማድረግ ነው፡፡

10/ “የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን” ማለት የህግ መተላለፍ የተፈጸመበት ወይም የተወረሰ ወይም የተተወ ዕቃ እስከሚወገድ ድረስ ተከማችቶ የሚቆይበት ቦታ ነው፡፡

11/ “ጨረታ” ማለት ኮሚሽኑ በሽያጭ የሚያስወግደውን ዕቃ ለመግዛት ተጫራቾች በግልጽ ወይም በሃራጅ ሽያጭ ሥርዓት የመወዳደሪያ ዋጋ የሚያቀርቡበት ነው፡፡

12/ “የግልጽ ጨረታ” ማለት ማንኛውም ተጫራች ለሽያጭ የቀረበን ዕቃ ለመግዛት ከመነሻ ዋጋ በመነሳት በራሱ አነሳሽነት በታሸገ እንቬሎፕ ወይም ፖስታ ተወዳዳሪ ዋጋ የሚያቀርብበት የጨረታ ዓይነት ነው፡፡



Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records Documentation No. 2

13/ "የሃራጅ ጨረታ" ማለት አንዱ ተጫራች ሌላው ያቀረበውን የመጫረቻ ዋጋ መነሻ አድርጎ የራሱን ዋጋ የሚያቀርብበት የጨረታ ዓይነት ነው፡፡

14/ "ልዩ ጨረታ" ከዕቃው ባህሪ አኳያ በመደበኛው የጨረታ ሥርዓት ቶሎ ሊወገድ እንደማይችል ሲገመት ያለ ቅድመ-ሁኔታ ለሽያጭ የሚቀርብበት አሰራር ነው፡፡

15/ "የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ (CIF)" ማለት የዕቃው የመሸጫ ዋጋ እና ከላኪ ሀገር እስከ መጨረሻ ወደብ ለዕቃው የተከፈለ ወይም የሚከፈል ወጪ እና ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የወጣ የኢንሹራንስ፣ የማጓጓዣ፣ የማስጫኛና የማውረጃ እንዲሁም የመንከባከቢያ ወጪ ድምር ነው፡፡

16/ "የኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ (FOB)" ማለት የዕቃው የመሸጫ ዋጋ እና ከላኪ ሀገር እስከ መጨረሻ ወደብ ድረስ ለዕቃው የተከፈለ ወይም የሚከፈል ወጪ ድምር ነው፡፡

17/ "ኮሚሽን" ማለት የጉምሩክ ኮሚሽን ሲሆን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችንም ይጨምራል፡፡

18/ "የመንግሥት የልማት ድርጅት" ማለት በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት ባለቤትነት ሥር የሚገኝ በአዋጅ የተቋቋመ የልማት ድርጅት ነዉ፡፡

19/ "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) ነው፡፡

20/ ሌሎች ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላት በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ጉምሩክ በሚያስወግደው ማንኛውም ዕቃ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የዕቃ አወጋገድ</u>

4. <u>ዕቃ ስለማስወገድ</u>

ኮሚሽኑ ፡-

1/ የተተወ ወይም የመጋዘን የቆይታ ጊዜ ያለፈበትን ወይም የተወረሰን ዕቃ በግልጽ ወይም በሃራጅ ወይም በልዩ ጨረታ ሊያስወግድ ይችላል፤

Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenue Records & Documentation No. 2

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም የገቢያ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች ከኮሚሽኑ ጋር ውል በተፈራረሙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የዕቃው የጨረታ መነሻ ዋጋ ክፍያ ተፈጽሞ ያስተላልፋል፤

3/ ለመንግሥት መሥሪያ ቤት አገልግሎት እንዲውል በገንዘብ ሚኒስቴር ውሳኔ የተሰጠበትን ዕቃ ለሚመለከተው መሥሪያ ቤት ያለ ክፍያ ያስተላልፋል፤

4/ የውጪ አገራት ገንዘብ ኖቶች በዕለቱ የምንዛሪ ተመን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስተላልፋል፤ የምንዛሬ ተመን ያልወጣለት ወይም ሊመነዘር የማይችል ወይም ሀሰተኛ የገንዘብ ኖት ለብሔራዊ ባንክ ያለክፍያ ያስተላልፋል፤

5/ ወርቅ እና ሌሎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀበላቸውን የከበሩ ማዕድናት በዕለቱ ዋጋ ለባንኩ ይተላለፋል፤

6/ ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚውሉ ዕቃዎችን አግባብነት ላላቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሊያስተላለፍ ያስተላልፋል፤

7/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ገንዘብ ሚኒስቴርን በማስፈቀድ ለተለያየ ችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመታደግ ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚውሉ ዕቃዎች ያለክፍያ እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ለነዚሁ መሥሪያ ቤቶች ማስተላለፍ ይችላል፤

9/ ከሚመለከተው አካል አገልግሎት ላይ እንዲውል ፈቃድ ያላገኘ በማውደም መወገድ የማይችል ዕቃ ወይም የተከለከለ ዕቃ ወይም በሽያጭ ሊወገድ የማይችል የከበረ ማዕድን ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ የመንግሥት አካላት ያለክፍያ ያስተላልፋል፤

10/ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ባለው ህግ መሠረት ቅርስ ሊባል የሚችል ዕቃ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

11/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በክፍያም ሆነ ያለክፍያ ለሌላ አካል ሊተላለፍ ወይም በገበያ ላይ ሊውል የማይችል ዕቃ እንዲሁም ለጤና ጎጂ የሆነ ወይም ከደረጃ በታች የሆነ ዕቃ በማውደም ያስወግዳል፤

ቤ.ትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን #1
Ethi... Customs Commission
...mentation No.1
Ethiopian Ministry of Re...
Records & Documentation No. 2

5. <u>የጨረታ ማስታወቂያ</u>

1/ ማንኛውም የጨረታ ማስታወቂያ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡

ሀ) የዕቃው መጠሪያ ስም፣ አይነት ወይም ሞዴል፣ ብዛት ወይም ክብደት ወይም መጠን፣ የምርት ዘመን፣ የሥሪት ሀገር፣ የኤሌክትሮኒክስ ሴሪያል ቁጥር እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች፣

ለ) ዕቃው ያለበት ሁኔታ (አዲስ / ያገለገለ / የተጎዳ ወይም ሌላ ሁኔታ) የሚገለጽ፣

ሐ) የዕቃው የጨረታ መነሻ ዋጋ፣

መ) ተጫራቾች በቅድሚያ የሚያስይዙት የዋስትና መጠን፣

ሠ) ዕቃው ወይም ናሙናው ለተጫራቾች እይታ የሚቀርብበት ቀን፣ ሰዓትና ቦታ፣

ረ) ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ ማሟላት ያለባቸው ግዴታ፣

ሰ) ዕቃዎቹን ለመሸጥ የተሻለ አማራጭ ወይም ዘዴ ከተገኘ መሥሪያ ቤቱ ጨረታውን መሰረዝ እንደሚችል የሚያመላክት መግለጫ፤

2/ ማንኛውም ጨረታ በአገሪቱ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባላቸው የህትመት እና/ወይም የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ለህዝብ ይፋ መደረግ አለበት፤

3/ የጨረታው ማስታወቂያ ፡-

ሀ) ለመጀመሪያ ጊዜ የሚወጣ ከሆነ ከጨረታ መክፈቻ ቀን ሰባት ቀን አስቀድሞ መውጣት አለበት፤

ለ) ለሁለተኛ ጊዜ የሚወጣ ከሆነ ከጨረታ መክፈቻ ቀን አምስት ቀን አስቀድሞ መውጣት አለበት፤

6. <u>የጨረታ ሰነድ</u>

ማንኛውም የጨረታ ሰነድ በጨረታ የሚሸጠውን ዕቃ የጨረታ መነሻ ዋጋ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሰ) የተመለከተውን ዝርዝር መረጃ የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡



በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

## 7. ተጫራቾች ማሟላት ያለባቸው ግዴታ

1/ ኮሚሽኑ በሚያወጣው የዕቃ ሽያጭ ጨረታ መወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች :-

ሀ) በዘርፉ የፀና የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የዘመኑን ግብር የከፈለ ለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

ለ) የዚህ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም ግምታዊ ዋጋው ከብር 500 ሺህ በታች የሆነ ማንኛውም ዕቃ ለመግዛት የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት ማቅረብ አያስፈልግም፡፡

ሐ) በዚህ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው ቅድመ-ሁኔታ ቢኖርም የሚሸጠው ዕቃ ተሽከርካሪ ሲሆን የተሽከርካሪው አስመጪ ወይም ባለቤትና ቤተሰብ ከሆነ ሰው በስተቀር ማንኛውም እድሜው ከ 18 አመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ ቅድመ-ሁኔታዎቹን ማሟላት ሳያስፈልገው በጨረታው ሊሳተፍ ይችላል፡፡

2/ በግልጽ ጨረታ ለመሳተፍ ዕቃውን ለመግዛት የሚያቀርበውን የመጫረቻ ዋጋ አምስት በመቶ (5%) ለጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም (C.P.O) በቅድሚያ ማስያዝ ይኖርበታል፤

3/ በሃራጅ ጨረታ ለመሳተፍ የዕቃውን የጨረታ መነሻ ዋጋ አምስት በመቶ (5%) ለጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም (C.P.O) በቅድሚያ ማስያዝ ይኖርበታል፤

4/ በዚህ መመሪያ መሠረት በሚከናወን ማንኛውም የጨረታ ሽያጭ የዕቃው አስመጪ ወይም ባለቤትና ቤተሰብ የነበሩ ሰዎች በጨረታው መሳተፍ አይችሉም፡፡

5/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የዕቃው ባለቤት እና ቤተሰብ" ማለት ዕቃውን በስሙ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም በህገወጥ መንገድ ይዞ የተገኘ ወይም ባለቤት የነበረ ሰው እና የዚሁ ሰው የትዳር ጓደኛ ወይም ልጆች ማለት ነው፡፡

6/ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚከናወን ጨረታ ያሸነፈ እንደሆነ ያሸነፈበትን የዕቃ ዋጋ በሙሉ ከፍሎ ዕቃውን በክፍል ሦስት በተገለጸው ጊዜ የመረከብ ግዴታ አለበት፡፡



በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን * 1 *
Ethiopi... Customs Commission
Rec... ...umentation No.1

8. <u>የጨረታ አፈጻጸም</u>

1/ ማንኛውም የጨረታ ሰነድ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ የኮሚሽኑ ማህተም ያረፈበት ሆኖ ለተጫራቾች በማይመለስ ብር 100 (አንድ መቶ) ይሸጣል፤

2/ በጨረታ የሚሸጠው ዕቃ ወይም የዕቃው ናሙና የጨረታው ማስታወቂያ በሚዲያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ጨረታው በሚካሄድበት ቦታ ላይ ለተጫራች ዕይታ ግልጽ ሆኖ ይቀርባል፤

3/ ኮሚሽኑ በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜ ሰዓትና ቦታ ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት የጨረታ ሳጥንና ቀጥሎም ተጫራቾች ዋጋ ያቀረቡባቸውን የጨረታ ሰነዶች ይከፍታል፤ የሃራጅ ጨረታ ሲሆን ሂደቱን ያስጀምራል፤

4/ ለግልጽ ጨረታው ዋጋ የቀረበባቸው ሰነዶች ከተከፈቱ በኋላ እያንዳንዱ ተጫራች ያቀረበውን የመጫረቻ ዋጋ ለተጫራቾች ይፋ ይደረጋል፤

5/ ማንኛውም በግልጽ ጨረታ የሚሳተፍ ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ዋጋ መቀየር ወይም የሌላ ተጫራችን ዋጋ ተንተርሶ ዋጋ አሻሽሎ ማቅረብ አይችልም፤

6/ ኮሚሽኑ ግልጽ ጨረታውን የሚያሰርዝ ምክንያት አለመኖሩን በማረጋገጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ይፋ ከተደረጉ የመጫረቻ ዋጋዎች መካከል ከፍተኛውን ዋጋ በመውሰድ የጨረታ አሸናፊውን በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ በጽሑፍ ለይቶ በመለጠፍ ያሳውቃል፤

7/ ጨረታው የሃራጅ ጨረታ በሚሆንበት ጊዜ ኮሚሽኑ የተጫራቾችን ብዛትና የቀረበውን ከፍተኛ ዋጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት ጨረታው የሚጠናቀቅበትን ጊዜና ዋጋ በአጫራቹ አማካኝነት ይወስናል፤

8/ የጨረታ ሽያጭ ሂደት በቃለ-ጉባዔ ተመዝግቦ መያዝ ይኖርበታል፡፡

9/ ኮሚሽኑ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ ሊሰርዝ ይችላል፤

12/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) መሠረት ጨረታ መሰረዝ የሚችለው የጨረታው አሸናፊ በደብዳቤ ከመገለጹ በፊት መሆን ይርበታል፡፡



የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን *1*
Ethiopian Customs Commission Records & Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

9. <u>ግልጽ ጨረታ</u>

1/ ማንኛውም ተጫራች የሚያቀርበውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋጋ የገለጸበትን ወይም የሞላበትን የጨረታ ሰነድ፣ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጹ ሰነዶች ኮፒ እና በንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸ የጨረታ ማስከበሪያ ቼክ ወይም (C.P.O) በእንቬሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ ለዚሁ በተዘጋጀው የኮሚሽኑ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለበት፤

2/ የጨረታ ሳጥኑ ከታሸገ በኋላ የሚመጡ የመጫረቻ ሰነዶች ተቀባይነት አይኖራቸውም፤

3/ የጨረታ ሳጥኑ በጨረታ ማስታወቂያ ሰነድ ላይ በተጠቀሰው ቦታ ቀንና ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ቢኖርም ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በቦታው ባይገኙም የጨረታ ሰነዱ በታዛቢዎች ፊት ይከፈታል፤

5/ ጨረታውን ያላሸነፉ ተጫራቾች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የጨረታው ውጤት ከተገለጸ በኋላ ባሉት ሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ይመለስላቸዋል፤

6/ የጨረታው አሸናፊ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዘው ገንዘብ በዕቃው የሽያጭ ዋጋ ላይ ተደምሮ ይታሰብለታል፤

10. <u>ሃራጅ ጨረታ</u>

ኮሚሽኑ፡-

1/ ጨረታን ለማስጀመር ቢያንስ በጨረታው ላይ ሁለት እና ከዚያ በላይ ተጫራቾች ሊገኙ ይገባል፤

2/ ለጨረታ የቀረበው ዕቃ የመነሻ ዋጋ የተወሰነለት ከሆነ የተወሰነውን መነሻ ዋጋ ገልጾ፤ ዋጋ ያልተወሰነለት ከሆነ ያልተወሰነለት መሆኑን ገልጾ ጨረታውን ያስጀምራል፤

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Customs Commission Records & Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

3/ በአጫራቹ አማካኝነት ተጫራቾች በጨረታው ሂደት የሚያቀርቡትን የዕቃ መግዣ ዋጋ ጎላ ባለ ድምፅ ወይም በድምፅ ማጉያ እያሰማ ጨረታውን ያስኬዳል፤

4/ በአጫራቹ አማካኝነት መጨረሻ ላይ የቀረበውን ከፍተኛ ዋጋ ጎላ ባለ ድምፅ እየጠራ ሌላ ከፍ ያለ ዋጋ የሚያቀርብ መኖር አለመኖሩን ጠይቆ በማረጋገጥ ይሄንኑ ዋጋ ከአንድ እስከ ሶስት በመቁጠር አሸናፊውን ገልጾ ጨረታውን ይዘጋል፤

5/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) የጨረታ ውጤት እንደተገለጸ ከአሸናፊው ጋር የሽያጭ ውል እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

11. ልዩ ጨረታ

1/ ኮሚሽኑ በጨረታ ሥርዓት ቶሎ ሊወገዱ እንደማይችሉ ወይም ለመንግሥት የልማት ድርጅት በክፍያ ሊተላለፉ የማይችሉ ጠቅላላ ዋጋቸው ከብር 100 ሺህ የማይበልጡ ዕቃዎች ለመሸጥ ፡-

ሀ) በማንኛውም ዘርፍ የወጣ የንግድ ፈቃድ ብቻ በመጠየቅ ሊሸጥ ይችላል፤ ሆኖም የዕቃዎቹ ዋጋ ከብር 30 ሺህ የማይበልጥ ከሆነ የንግድ ፈቃድ ሳይጠይቅ ሊሸጥ ይችላል፤

ለ) የዕቃውን ዓይነት፣ ብዛትና ዋጋ የያዘ የዕቃ ሽያጭ ማስታወቂያ በመሥሪያ ቤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ብቻ በመለጠፍ ሊሆን ይችላል፣

ሐ) የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና አይጠይቅም፤

2/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በልዩ ሁኔታ በጨረታ የሚሸጥ ዕቃ ተወዳዳሪ ተጫራች ባይኖርም ለቀረበው ብቸኛ ተጫራች ሊሸጥ ይችላል፤

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በልዩ ሁኔታ በጨረታ ለሚሸጥ ዕቃ የጨረታ አሸናፊ ገንዘቡን ወዲያውኑ ከፍሎ ዕቃውን መረከብ ይኖርበታል፤

4/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በልዩ ጨረታ የሚሸጡ ዕቃዎችን ዓይነት እና ዋጋ በተተው እና የተወረሱ ዕቃዎች አወጋገድ ሥራ ሂደት አቅራቢነት በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ እየተወሰነ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission Records & Documentation No.1
በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

12. <u>የጨረታ መነሻ ዋጋ አተማመን</u>

1/ የዕቃዎች ጨረታ መነሻ ዋጋ በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን ሥርዓት በተለይም በሚዛናዊ ዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዕቃዎቹ ባሉበት ወቅታዊ ሁኔታ ተመሥርቶ የሚሠራ ይሆናል፤

2/ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚወጣ የዕቃ ሽያጭ የጨረታ መነሻ ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደዉ ለገቢ ዕቃ የዕቃው የሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ እና ቀረጥና ታክስ ከሁለቱ የሚበልጠው ይሆናል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ዕቃው በግልጽ ጨረታ ያልተሸጠ እንደሆነ ዕቃው ለሁለተኛ ጊዜ ለግልጽ ጨረታ ሲቀርብ የጨረታ የመነሻ ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደው በመጀመሪያው ግልጽ ጨረታ የመነሻ ዋጋ ተደርጎ የተወሰደው የዕቃው የሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ ከሆነ ከኤፍ.ኦ.ቢ /FOB/ ዋጋ እና ከቀረጥና ታክስ ከሁለቱ የሚበልጠው ሲሆን ተወስዶ የነበረው ቀረጥና ታክስ ከሆነ ደግሞ የሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ ይሆናል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ዕቃው በሃራጅ ጨረታ ያልተሸጠ እንደሆነ ዕቃው ለሁለተኛ ጊዜ ለሃራጅ ጨረታ ሲቀርብ የጨረታ መነሻ ዋጋ ሳይወሰንለት በድጋሚ ለሃራጅ ጨረታ ይቀርባል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መነሻ ዋጋ መሠረት በግልጽ ጨረታ ሊሸጥ ያልቻለ ዕቃ የመነሻ ዋጋ ሳይወሰንለት ለሃራጅ ጨረታ ይቀርባል፤

6/ በህገወጥ መንገድ ከአገር ሊወጡ ሲሉ የተያዙና የተወረሱ ዕቃዎች የጨረታ መነሻ ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደው የአገር ውስጥ ወይም የአካባቢው የወቅቱ አማካኝ የገበያ ዋጋ ይሆናል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ተጠንቶ የሚቀርብ የአካባቢ የገበያ ዋጋ በሥራ ሂደት አስተባባሪ ወይም በሚመለከተው ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ መፅደቅ ይኖርበታል፡፡

Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

## ክፍል ሦስት

## የዕቃዎች ርክክብና የሽያጭ ገንዘብ ገቢ አሰባሰብ

### 13. የሽያጭ ገቢ አሰባሰብና የዕቃ ርክክብ ጊዜ

1/ የጨረታው አሸናፊ ጨረታውን ስለማሸነፉ ከተገለጸለት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ቀናት ውስጥ ያሸነፈበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ በማድረግ ዕቃውን መረከብ አለበት፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተፈጻሚ ካልተደረገ ለጨረታ ማስከበሪያ የተያዘው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ሆኖ ዕቃው በድጋሚ ለሽያጭ ይቀርባል፤ ሆኖም ዕቃው ያልተነሳው በአሳማኝ ምክንያት ከሆነ የሥራ ሂደት አስተባባሪው ይሄንኑ ከግምት በማስገባት ጊዜውን ለተጨማሪ ሶስት ቀናት ሊያራዝም ይችላል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለጸው ቢኖርም አሸናፊው ያሸነፈበትን የዕቃ ዋጋ ገቢ አድርጎ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ያላነሳ እንደሆነ ለሚቆይበት ተጨማሪው ጊዜ የመጋዘን ኪራይ ይከፍላል፡፡ ሆኖም ዕቃው በሁለት ወር ውስጥ ካልወጣ እንደተተወ ተቆጥሮ በሽያጭ ይወገዳል፡፡

4/ ዕቃው በክፍያ የተላለፈለት የመንግሥት የልማት ድርጅት ከሆነ የልማት ድርጅቱ ዕቃውን እንዲረከብ ማስታወቂያ በደረሰው በአሥር ቀናት ውስጥ ተገቢውን ክፍያ ፈጽሞ ዕቃውን ከመጋዘን ተረክቦ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

5/ የልማት ድርጅቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢውን ክፍያ ፈጽሞ ዕቃውን ያላነሳ እንደሆነ የማስተላለፍ ሂደቱን ተቋርጦ ዕቃው በሌላ መንገድ ይወገዳል፡፡

## ክፍል አራት

## ተግባርና ኃላፊነት

### 14. የሥራ ሂደት ተግባርና ኃላፊነት

1/ የተወረሰ፣ የተተወ እና በመጋዘን ቆይታ ጊዜ ገደብ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፈጽመው ያልወጡ ዕቃዎችን መረጃ አደራጅቶ መያዝ እና ዕቃዎቹን የማስተዳደር፤



Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenue Records & Documentation No. 2

2/ ለሽያጭ የሚቀርቡ ዕቃዎች በመለየት ዋጋ የመተመን፤

3/ የጨረታ ሰነድ የማዘጋጀት፣ የማስታወቂያ የማስነገር፣ ጨረታውን የማከናወን፣ የሽያጭ ገንዘብ ገቢ እንዲሆን የመከታተል እና ዕቃዎችን ለገዥዎች የማስረከብ፤

4/ በማውደም የሚወገዱት ዕቃዎችን የሚመለከታቸው የተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቶች ተወካዮች እና/ወይም የህግ አስከባሪ አካላት እንዲገኙ በማድረግ የማስወገድ፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (4) መሠረት ዕቃ ለማስወገድ የሚያስፈልገው ወጪ እንደሁኔታው በዕቃው ባለቤት ወይም በኮሚሽኑ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

6/ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት እና ለሰብዓዊ እርዳታ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን መረጃ አደራጅቶ ለትራንዚት እና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የማቅረብ፤ ሲወሰንም ለሚመለከታቸው አካላት የማስተላለፍ፤

7/ ሌሎች በማስተላለፍ ሊወደዱ የሚገባቸውን ዕቃዎች ለሚመለከታቸው አካላት በሰነድ ርክክብ ፈጽሞ የማስተላለፍ፤

8/ እንደተሽከርካሪ ላለ የስሙ-ንብረት ዝውውር ለሚፈልግ የተሸጠ ዕቃ የተሸጠበት ዋጋ ቀረጥና ታክስ እንደተከፈለ ተቆጥሮ ለገዥው ዜሮ ዲክላራሲዮን እንዲዘጋጅለት የማድረግ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

9/ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በሽያጭ ለሚወገዱ ዕቃዎች በእያንዳንዱ ጨረታ አራት የአስወጋጅ ኮሚቴ አባላት የሚኖሩት ሲሆን የተተው እና የተወረሱ ዕቃዎች አወጋገድ ሥራ ሂደት አስተባባሪ እና የዕቃ አስወጋጅ ቡድን አስተባባሪ እንደቅደም ተከተላቸው ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ሲሆኑ የተቀሩት የዕቃ አስወጋጅ ቡድን ባልደረቦች ይሆናሉ፡፡

15. <u>የዳሬክቶሬቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የትራንዚት እና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ፡-

1/ ዕቃዎችን በተቀላጠፈ መንገድ ለማስወገድ የግዥና ሽያጭ ውል እና የመግባቢያ ስምምነት ለማድረግ የሚያስችል የውሳኔ ሃሳብ ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ ያቀርባል፤



በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission Records & Documentation No.1
Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

2/ የዕቃ ሽያጭ ማስታወቂያ ውሎች ከህትመት እና ከኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎች ጋር እንዲደረግ ይከታተላል፤

3/ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት እና ለሰብዓዊ እርዳታ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን መረጃ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር በማሰባሰብ አደራጅቶ ለበላይ አመራር ያቀርባል፤

16. የተሻረ መመሪያ

የተተው እና/ወይም የተወረሱ ዕቃዎች አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 122/2009 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

17. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ተፈርሞ ከመውጣቱ በፊት በሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮች በቀድሞ መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

18. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

የካቲት ----- ቀን 2012 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

አዳነች አቤቤ

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenue
Records & Documentation No. 2